የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፫

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No.25
ADDIS ABABA, 8th April, 2021


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፬/፪ሺ፲፫

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኡጋንዳ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ……………ገጽ ፲፫ሺ፪፻፳፬


## Content


Proclamation No. 1244/2021

Extradition Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Uganda Ratification Proclamation…………..…………..page13224


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፬/፪ሺ፲፫

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኡጋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኡጋንዳ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በወንጀል ጉዳዬ የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት ነሐሴ ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በካምፓላ የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱን ማጽደቅ ወንጀል ፈጽመው የኮበለሉ ግለሰቦችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችል በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ባካሄደው ፲፪ኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1244/2021

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE EXTRADITION AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF REPUBLIC OF UGANDA**

**WHEREAS,** the Extradition Agreement between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the government of Republic of Uganda has been signed in Kampala, on the 16th day of August, 2019;

**WHEREAS,** ratifying the the treaty enables to bring fugitives to justice;

**WHEREAS**, the House of Peoples'Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Extradition Agreement at its 12th Regular session held on 24th day of March ,2021,

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኡጋንዳ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፵፬/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኡጋንዳ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ነሐሴ ፲ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በካምፓላ የተፈረመው በወንጀል ጉዳች የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከሌሎች ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱን የማስፈጸም ስልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

**NOW,THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Extradition Agreement between the government of Federal Democratic Republic of Ethiopia and the governmet of Republic of Uganda Ratification Proclamation No.1244/2021".

## 2. Ratification of the Agreement

The Extradition Agreement signed in Kampala on the 16th day of August, 2019 between the government of Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Uganda is hereby ratified.

## 3. Responsibility of the Attorney General

The Attorney General of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby authorized to follow up the implementation of the Agreement in collaboration with other relevant government organs.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 8th Day of April,2021**

**SAHLEWORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**